የእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ፣ የስነፅሁፍና፤ የሂሳብ ፈተናዎች "የኮሌጁና የሥራ ዝግጁነት ምዘና ሽርከና" **"Partnership for Assessment of Readiness for College and Career (PARCC )"** ውጤት ዘገባን መገንዘብ:-

ስለ ሜሪላንድ ኮሌጅ እና የሥራ ዝግጁነት መስፈርቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ የስነጥበብ/መሠረተ ትምህርት እና ሂሳብ PARCC ግምገማ ሲደረግ የ2017–2018 የትምህርት ዓመት ለአራተኛ ጊዜ ነበር። ፈተናዎቹ፣ በአንክሮ ትንታኔና በፅሁፍ ላይ በማተኮር፣ ሂሳዊ አስተሳሰብንና ፕሮብሌም አፈታትን የመሳሰሉ ውስብስብ ክሂሎቶችን ይመዝናሉ። የ PARCC ግምገማዎች ሲካሄዱ ከተማሪዎች የሚጠበቀው ምንባብ፣ ጽሑፍ፣ እና ሃሳብ መስጠት፣ ትንታኔ እና ውጤትን ማሳየት፣ እና በተጨባጩ ዓለም ነባራዊ ሁኔታ ከበርካታ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችም/ኢንፎርሜሽን ጥቅም ላይ ማዋል ነው። ስለተማሪ እርምጃ ግልጽ የሆነ ስዕል ለማግኘት ተማሪው/ዋ ተፈላጊውን የአካደሚክ መስፈርት ማሟላቱን/ማሟላቷን ለማረጋገጥ የ PARCC ውጤቶች ከተማሪው/ዋ የክፍል ትምህርት አፈፃፀም፣ የሪፖርት ካርድ ውጤቶች፣ እና የመምህር/ት አስተያየት ጋር አብሮ መታየት አለበት።

የተማሪዎን የውጤት ዘገባ የማንበብ ዘዴ:-

1. አጠቃላይ አፈፃፀም:- ተማሪዎች ከአምስቱ የአፈፃፀም ደረጃዎች በአንዱ ላይ በመመስረት በያንዳንዱ ርእስ አጠቃላይ ውጤት ያገኛሉ። የአፈፃፀም ደረጃዎቹ አንድ ተማሪ ላለ(ች)በት የክፍል ደረጃ የሚመጥን የውጤት ደረጃ ገና ብቃት እንደሌለው ከሚያመለክተው ደረጃ 1 አንስቶ ተማሪው/ዋ የክፍሉን ተፈላጊ የውጤት ደረጃ አልፎት መሄዱ(ዷ)ን እስከሚያመለክተው እስከ ደረጃ 5 ይደርሳል።

2. የውጤት ገደብ:- - ይህ መለኪያ የያንዳንዱን የአፈፃፀም ደረጃ ውጤት ገደብ "ከ  እስከ" ያካትታል። እናም የልጅዎን ውጤት በዚያ ገደብ ውስጥ የትኛው ደረጃ ላይ እንደሚ(ምት)ገኝ ያሳያል።

3. ለኮሌጅና ሥራ ዝግጅት:- ከ 4 ወይም 5 ነጥቦች ተፈላጊ የማርክ ደረጃ ወይም ከሚፈለገው በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲመረቁ ለኮሌጅ ደረጃ የኮርስ ስራ ዝግጁ ናቸው።

4. አጠቃላይ የውጤት ንጽጽር:- እዚህ ላይ ልጅዎ በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ፣ በሚማርበት/በምትማርበት ት/ቤት፣ በትምህርት ዲስትሪክቱ ከዳር እስከዳር፣ እና ከስቴቱ አጠቃላይ ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር የትምህርት አፈፃፀሙ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያሳያል። በተጨማሪም የተማሪን ግላዊ ችሎታ ለመመዘን በተለያዩ የአፈፃፀም ደረጃዎች የሚገኙ የተማሪዎች መቶኛን/ፐርሰንቴጅ እና ተማሪ በግል የሚያሳየውን የችሎታ እድገት በመቶኛ/ፐርሰንቴጅ ይዘረዝራል።



## የተማሪዎን የውጤት ዘገባ የማንበብ ዘዴ ቀጣይ...

**5.** ምንባብ/ጽሑፍ አፈፃፀም:- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ ዘገባ የተማሪዎን የምንባብና የመፃፍ ንፅፅር ውጤት ያመለክታል። በዚህ ንዑስ ክፍል በሚገኙ ጥያቄዎች ተማሪዎ ያስመዘገበ(ች)ውን ውጤት በቁጥር ያመለክታል። ለማጣቀሻ ያህል ተማሪዎ ካስገኘ(ች)ው ግላዊ ውጤት በተጨማሪ የውጤት "ከ-እስከ" ገደብ ተገልጿል። ይህኛው ን/ክፍል የት/ቤቱን፣ የዲስትሪክቱን፣ እና የስቴቱን አማካይ ውጤቶች በተጨማሪ ያካትታል።

**6.** የውጤት ዝርዝር:- ተማሪዎ በየትኛው ትምህርት ጥሩ ውጤት ላይ እንደሚገኝ/እንደምትገኝ ወይም ማሻሻል ያለበትን ለማየት እንድትችሉ የውጤት ዘገባው በዝርዝር በተወሰኑ ከሂሎቶች ተተንትኗል። እያንዳንዱ የተማሪዎን ውጤት ተፈላጊውን የክፍል ደረጃ ውጤት ካስመዘገቡ ተማሪዎች ጋር ለማወዳደር በቀስት ያሳያል። የሚማርበትን ክፍል ደረጃ ብቃት/ከሂሎቶች የሚገልጽ የውጤት-ደረጃ ግንዛቤ የሚያሳይ የከሂሎቶች ገለፃም በተጨማሪ ተካትቷል።







marylandpublicschools.org
marylandassessments.org

### የግምገማና የፈተና እውነታ በሜሪላንድ:-

- የፌደራል ህግ ከ3ኛ-8ኛ ክፍሎችና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች አመታዊ ስቴት-አቀፍ ፈተና/ምዘና እንዲወስዱ ይጠይቃል።
- የሜሪላንድ ምሁራን፣ ፈተናዎችን ከመተንተን እና ማሻሻያ/ለውጥ በማድረግ አግባብነት በፈተናዎቹ መዳበርና መሻሻል ላይ እጅጉን ይሳተፋሉ። የፈተናዎቹን አቅጣጫ ለመምራት በማገዝ፣ ሜሪላንድ የPARCC አስተዳደር ቦርድ አባል ናት።
- የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ወላጆች ለግል የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም "IEP" ወይም 504 ቡድኖች ጋር ስለተፈቀዱ መገልገያዎች እና አመቺ ስፍራ መነጋገር አለባቸው።
- ውጤቶቹ የሚያመለክቱት በትምህርት አመት መጨረሻ የተማሪው/ዋ የክፍል-ደረጃ ትምህርት ግንዛቤ መመዘኛዎችን ነው።
- የውጤት ዘገባዎች የሚያገለግሉት:- መመህራን የዳበረ የማስተማር እቅድ አዘጋጅተው ተማሪዎችን ለሚመጣው የትምህርት አመት ወደሚቀጥለው እርከን ለማዘጋጀት የሚያቅዱባቸው መሳርያዎች ናቸው።
- ቤተሰቦች ስለልጃቸው አካዴሚያዊ ጥንካሬና ማሻሻል ስላለበት ሁኔታ ከልጃቸው መምህራንና የት/ቤት ሃላፊዎች ጋር ውይይት ለመጀመር በነዚህ ውጤቶች መጠቀም ይችላሉ።
- በት/ቤትም ሆነ በመኖርያ ቤት የልጁን/የልጅቱን የትምህርት ፍላጎት በይበልጥ እንዴት መደገፍ እንደሚቻል እያንዳንዱ አብሮ መወሰን ይችላል።

### ኢጋዥ ድረ-ገጾች

- Understand the Score- http://understandthescore.org/en•espanol/
- Be a learning hero- http://bealearninghero.org/learning-tools/#results
- Great Kids- greatschools.org/gk/common-core-test-guide
- PARCC practice tests- parcc.pearson.com/practice-tests
- Achieve resources on standards- achieve.org/files/ResourcesforParentsandFamiliesonCCSSv2.pdf